# ሀገር አቀፍ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ኢንስፔክሽን ማዕቀፍ

መጋቢት 2007 ዓ.ም.

ትምህርት ሚኒስቴር

## ማውጫ ገፅ


1 መግቢያ:- ---------- 2

2 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዓላማዎች ---------- 3

2.1 አጠቃላይ ዓላማ---------- 3

2.2 ዝርዝር ዓላማዎች ---------- 3

3 አስፈላጊነት---------- 3

4 የኢንስፔክሽን መሪ መርሆዎች ---------- 4

5 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት የኢንስፔክሽን መለኪያዎች ፣ የትኩረት መስኮች ፣ ስታንዳርዶችና አመልካቾች ---------- 4

5.1 ግብዓት /Input/---------- 5

5.2 ሂደት /Process/ ---------- 6

5.3 ውጤት /Output /---------- 9

6 የኢንስፔክሽን ሂደት ---------- 10

6.1 ለኢንስፔክሽን ተግባር የጣቢያዎች አመራረጥ ---------- 10

6.2 የኢንስፔክሽን ቡድን አመሰራረት---------- 10

6.3 ከኢንስፔክሽን በፊት ከጣቢያዎች ጋር የሚደረግ ግንኙነት---------- 10

6.4 የኢንስፔክሽን አተገባበር ---------- 11

6.5 የመረጃ አሰባሰብ ሂደት---------- 11

6.6 የመለኪያዎች ክብደት አሰጣጥ ---------- 11

6.7 የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት---------- 12

6.8 ግብረ መልስ ስለ መስጠት---------- 13

6.9 የጽሁፍ ሪፖርት---------- 13

6.10 ድጋፍና ክትትል ስለማድረግ ---------- 14

6.11 የቅሬታ አቀራረብ ---------- 14

7 የኢንስፔክተሮች ሙያዊ ስነ-ምግባር ---------- 14

ተቀጽላ-1 (APPENDIX) የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ኢንስፔክሽን ስታንዳርዶችና አመልካቾች ---------- 16

ተቀጽላ-2 ፥ ገላጮች / DESCRIPTORS / ---------- 21

ተቀጽላ 3 (APPENDIX –III) የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ቀመር ምሳሌ__________ 37

ተቀጽላ 4 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ኢንስፔክሽን ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ---------- 41

## 1 መግቢያ:-

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ሀገራችንን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለማሰለፍና ፈጣን ዕድገት ለማስመዝገብ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን ነድፎ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። በዚህም መሰረት ትምህርት ለልማት፣ ለዲሞክራሲና ለመልካም አስተዳደር ግንባታ ቁልፍ ሚና የሚጫወት መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለዘርፉ ዕድገት ልዩ ትኩረት ተሰጥቷል:: ስለሆነም በእውቀት፣ በክህሎት፣ በአመለካከት እና በመልካም ስነ-ምግባር የታነጸ ብቁ ዜጋ ለማፍራት የሚያስችል የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ተቀርፆ ስራ ላይ ከዋለ ዓመታት ተቆጥረዋል። በክልሎች ያለውንም የትምህርት ተደራሽነትና ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ የተለያዩ ስትራቴጂዎች ተቀይሰዋል። ከተቀየሱትም ስትራቴጂዎች መካከልም አንዱ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ነው። በዚህም ስትራቴጂ በመደበኛው የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሳይክል ትምህርት የመማር ዕድል ላላገኙ ህጻናት የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት በስራ ላይ እንዲውልም ተደርጓል።

በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ የሚሰጠው ትምህርት ጥራቱን የጠበቀና ተማሪዎችን ለቀጣይ የትምህርት ደረጃ በብቃት የሚያዘጋጅ መሆን ይገባዋል። በመሆኑም ጣቢያዎች በግብዓት፣ በሂደትና በውጤት ያሉበትን ደረጃ ከተቀመጠው ስታንዳርድ አኳያ በመመዘን የሚሻሻሉበትን ስርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። በመሆኑም የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች አፈፃፀምን ለመከታተል የሚያስችል ይህ ሀገር አቀፍ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ኢንስፔክሽን ማእቀፍ ተዘጋጅቷል። ማዕቀፉ በውስጡ መግቢያ፣ አላማ፣ አስፈላጊነት፣ መሪ መርሆዎች፤ ስታንዳርዶችና ከኢንስፔክተሮች የሚጠበቅ ስነ-ምግባር አካቶ ይዟል።

# 2 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዓላማዎች

## 2.1 አጠቃላይ ዓላማ

የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዋና ዓላማ የትምህርት ተደራሽነትን፣ ፍትሃዊነት፣ አግባብነትና ጥራትን በማረጋገጥ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተማሪዎችን ውጤትና ሥነ-ምግባር ማሻሻል ነው።

## 2.2 ዝርዝር ዓላማዎች

- አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች የሚጠበቅባቸውን ዝቅተኛ ተፈላጊ ደረጃ (Minimum standard) ከግብዓት፣ ከሂደትና ከውጤት አንፃር ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ፣
- በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች የሚሰጠው ትምህርት ለደረጃው የተቀመጠውን ስታንዳርድ አሟልቶ ውጤት ማስመዝገብ እንዲችል አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግና ውጤታማነቱን ለማረጋገጥ፣
- ባለድርሻ አካላት የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች ስላሉበት ደረጃ በመከታተልና መሻሻል በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ተሳትፏቸው መጎልበቱን ለማረጋገጥ፣
- የሚሰጠው ትምህርት ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ መሆኑን በማረጋገጥ ያለበትን ደረጃ ለይቶ ለማወቅና ተጨማሪ ድጋፍ ለማድረግ፣
- በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት አተገባበር ላይ ወቅታዊና ተአማኒነት ያለውን መረጃ በማሰባሰብ የማሻሻያ ሀሳብ ለመስጠት ፣

# 3. አስፈላጊነት

የሀገር አቀፍ አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ኢንስፔክሽን ሥርዓት ዘርግቶ ስራ ላይ ማዋል የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል።

- የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎችን ወጥ በሆነ መለኪያ በመመዘን በዘርፉ የትምህርት ጥራትን በሀገር አቀፍ ደረጃ ለማረጋገጥ፣
- የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያዎችን ከግብአት፣ ከሂደት እና ከውጤት አኳያ በመመዘን ደረጃ ለመስጠት፣
- በጣቢያዎች መካከል የሚደረገውን በጎ ፉክክር በማጎልበት የተሻለ አፈፃፀምና ውጤት ያላቸውን ለበለጠ ስኬት እንዲተጉ ለማበረታታትና ተሞክሯቸውን ቀምሮ ለማስፋት ፣
- ዝቅተኛ አፈፃፀምና ውጤት ያስመዘገቡ ጣቢያዎችን ድክመታቸውን በግልፅና በማያሻማ መንገድ በመጠቆም እንዲሻሻሉ ለማድረግ ፣

- የተጠያቂነት ስርአት በየደረጃው ለማስፈን፣
- ጣቢያዎች ያሉበትን የአፈፃፀምና የውጤት ደረጃ የሚያሣይ መረጃ ለባድርሻ አካላት ለመስጠትና የተደራጀ የመረጃ ስርዓት ለማስፈን፣

## 4. የኢንስፔክሽን መሪ መርሆዎች

የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ኢንስፔክሽን ሂደት የሚከተሉትን መሠረታዊ መሪ መርሆዎችን ይከተላል። እነርሱም፡-

- ነጻ ወይም የጣቢያው አካል ባልሆኑ የትምህርት ኢንስፔክተሮች ይካሄዳል፣
- የአንድን አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ ለመገምገም ተጨባጭ፣ ወጥነትና ቀጣይነት ባላቸው መረጃዎች ላይ ተመስርቶ ይካሄዳል፣
- ግምገማው ሁሉንም የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ባካተተ መልኩ በተቀመጡት ግልጽ ስታንዳርዶችና መስፈርቶች መሠረት የሚካሄድ እንጂ የኢንስፔክተሮች ግላዊ አመለካከት ፈጽሞ አይንጸባረቅበትም ፣
- ገንቢ እና ለጉዳዮች ትኩረት የሚሰጥ፤የተከናወኑ መልካም ተግባራትን የሚያበረታታና እጥረቶችን ለይቶ በማውጣት የማሻሻያ ሃሳብ የሚሰጥበት ተግባር ነው፣
- የጣቢያውን ማህበረሰብ ስብእና በማክበር ይከናወናል፣
- የግምገማ ተግባራት ጣቢያዎች እንደ ተቋም ባስመዘገቡት ውጤት ላይ ያተኮረ እንጂ በግለሰቦች የሥራ አፈጻጸም ላይ መሆን አይገባውም።

## 5. የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት የኢንስፔክሽን መለኪያዎች ፣ የትኩረት መስኮች ፣ ስታንዳርዶችና አመልካቾች

የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ኢንስፔክሽን ሶስት መለኪያዎች ያሉት ሲሆን እነርሱም ግብዓት፣ ሂደት እና ውጤት ናቸው። መለኪያዎቹና በስራቸው የተካተቱ የትኩረት መስኮች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

| መለኪያዎች | የትኩረት መስኮች |
|---|---|
| ግብዓት | 1. የጣቢያው ፋሲሊቲ፣ የመማሪያና የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች፣ የሰው ኃይልና የገንዘብ ምንጮች |
| | 2. ምቹ የመማሪያ አካባቢ |
| ሂደት | 3. ሥርዓተ ትምህርት፣ መማር፣ ማስተማር፣ ምዘና |
| | 4. ጣቢያው ከወላጆችና ከህበረተሰቡ ጋር ያለው ግንኙነት |
| ውጤት | 5. የተማሪዎች ውጤትና ሥነ-ምግባር |

## 5.1 ግብዓት /Input/

### 5.1.1 የጣቢያው ፋሲሊቲ፣ የመማሪያና የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች ፣ የሰው ኃይልና የገንዘብ ምንጮች

**ስታንዳርድ 1**

ጣቢያው ለደረጃው በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የመማሪያና የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፣ የማስፈጸሚያ ሰነዶች፣ የመጫወቻ ቁሳቁሶች አሟልቷል።

**አመልካቾች፡-**

- የጣቢያው የመማሪያና አገልግሎት መስጫ ክፍሎች በተቀመጠላቸው ስታንዳርድ መሰረት ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ማስተናገድ በሚችል መልኩ (በቂ ብርሃን፣ ስፋት፣ወለል ወዘተ) የተሰሩና የተሟሉ ናቸው፣
- ጣቢያው በስታንዳርዱ መሰረት የተማሪ መጽሐፍት ጥምርታ ፣ የተማሪ-ክፍል ጥምርታ፣ የተማሪ-አመቻች ጥምርታ፣ የአመቻቹ/ቿ መምሪያ ፣ አጋዥ/ ማጣቀሻ መጽሐፍትና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን አሟልቷል፣
- በጣቢያው ሀገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ ልዩ ልዩ መመሪያዎች፣ ሀገራዊና ክልላዊ ፕሮግራሞችና ማዕቀፎች፣ የጣቢያው ደንብ ወዘተ ተሟልቷል፣
- ጣቢያው በስታንዳርዱ መሠረት የመጫወቻ ቦታ፣ ቁሳቁሶች እና ሌሎች ፋሲሊቲዎችን አሟልቷል።

**ስታንዳርድ 2**

የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማሻሻል ጣቢያው አስፈላጊ የሃብት ምንጮች አሰባስቧል።

**አመልካቾች፡-**

- ጣቢያው የድጎማ በጀቱን (School grant) ተቀብሏል፣
- ጣቢያው ጥቅል በጀቱን (Block grant) ተቀብሏል፣
- ጣቢያው ከወላጆችና ከአካባቢው ማህበረሰብ ሃብት (በገንዘብ፣ በዓይነትና በጉልበት) አሰባስቧል፣
- ጣቢያው በአካባቢው ከሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ሃብት አሰባስቧል፣

**ስታንዳርድ 3**

ጣቢያው ለደረጃው የሚመጥኑ ተጠሪ አመቻችና አመቻቾች በስታንዳርዱ መሰረት አሟልቷል።

**አመልካቾች፡-**

- ጣቢያው በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ማስረጃ ያለው/ያላት ተጠሪ አመቻች አለው፣
- ጣቢያው በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ማስረጃ ያላቸው አመቻቾች አሉት።

### 5.1.2. ምቹ የመማሪያ አካባቢ

**ስታንዳርድ 4**

*ግቢያው ለህፃናቱ ቅርብ፣ ምቹና ለደህንነታቸው የማያሰጋ ነው።*

**አመልካቾች ፡-**

- የትምህርት መስጫ ግቢያውን ማስከበር የሚችል አጥር ተሰርቷል፣
- ግቢያው በስታንዳርዱ መሠረት ተፈላጊውን የቦታ ስፋት አሟልቷል፣
- በግቢያው የሚገኙ የመማሪያ ክፍሎችና አገልግሎት መስጫዎች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን አካቶ ለማስተማር ምቹ ነው፣
- ግቢያው ለህፃናት ምቹና የመማር ማስተማሩን ሂደት ከሚያውኩና በህፃናት ላይ አደጋ ሊያስከትሉ ከሚችሉ (አውሬ፣ ገደል፣ ጎርፍ. ወዘተ…) የራቀ ነው፣
- ግቢያው በፆታ የተለየ መፀዳጃ ቤት አለው፣
- ግቢያው የውሃ አገልግሎት አለው።

## 5.2 ሂደት /Process/

### 5.2.1 ሥርዓተ ትምህርት፣ መማር ፣ ማስተማር ፣ምዘና

**ሥርዓተ ትምህርት**

**ስታንዳርድ 5**

በግቢያው የሚሰጠው ትምህርት በአገር አቀፍ ወይም በክልሉ በተዘጋጀው የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት / በመደበኛው ሥርዓተ ትምህርት መሰረት ነው።

**አመልካቾች ፡-**

- ግቢያው የሚጠቀምበት የተማሪዎች መፅሐፍትና የአመቻቾች መምሪያ ሥርዓተ ትምህርቱን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ነው፣
- አመቻቾች የሚያስተምሩት ትምህርት በሥርዓተ ትምህርቱ መሰረት ነው።

**መማር**

**ስታንዳርድ 6**

ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ንቁ ተሳትፎ አድርገዋል።

**አመልካቾች፡-**

- ተማሪዎች የተሰጧቸውን ሥራዎች በትጋት ይሰራሉ፣
- ተማሪዎች ጥያቄዎችን በመጠየቅና መልሶችን በመመለስ የነቃ ተሳትፎ አድርገዋል፣
- ተማሪዎች በተለያዩ አደረጃጀቶች በመሳተፍ እርስ በርስ ተደጋግፈዋል።

**ስታንዳርድ 7**

ተማሪዎች በትምህርት አቀባበላቸው መሻሻል አሳይተዋል።

**አመልካቾች፡-**

- ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እየተማሩ ነው፣
- ተማሪዎች የትምህርት ጊዜያቸውን ሳያባክኑ በአግባቡ ተጠቅመዋል፣
- የክፍል ደረጃውን የሚመጥን የእጅ ጽሁፍ፣ የማንበብና የመሠረታዊ ስሌት ችሎታ አላቸው፣
- ተማሪዎች ለሚማሯቸው ትምህርቶች ተመጣጣኝ ክብደት ይሰጣሉ።

**ማስተማር**

**ስታንዳርድ 8**

የጣቢያው ትምህርት ፕሮግራም አደረጃጀት በተቀመጠው ስታንዳርድና የአካባቢው ህብረተሰብ አኗኗርን ያገናዘበ ነው።

**አመልካቾች፡-**

- የጣቢያው ዓመታዊ፣ ሳምንታዊና ዕለታዊ የትምህርት ፕሮግራም በስታንዳርዱ መሰረት የተዘጋጀ ነው፣
- የትምህርቱ አሰጣጥ የህብረተሰቡ አኗኗርን መሰረት ያደረገ ነው ።

**ስታንዳርድ 9**

አመቻቾች የሚያስተምሩት ትምህርት በአግባቡ የታቀደና በትምህርት መርጃ መሳሪያዎች የተደገፈ ነው።

**አመልካቾች፡-**

- አመቻቾች ትምህርቱን በዓመት፣ በሴሚስተር፣ በሣምንት/ በቀንና በክፍለ ጊዜያት/ ከፋፍለው አቅደዋል፣
- አመቻቾች ከትምህርቱ ይዘት ጋር የተጣጣመ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ተጠቅመዋል፣
- አመቻቾች ተማሪዎቻቸው በትምህርታቸውና በውጤታቸው እንዲሻሻሉ የማጠናከሪያ ትምህርት በመስጠት እገዛ አድርገዋል፣
- አመቻቾች ለሴት ተማሪዎች የተለየ እገዛ አድርገዋል።

**ስታንዳርድ 10**

አመቻቾች አሳታፊ የማስተማር ዘዴ ተጠቅመዋል።

**አመልካቾች፡-**

- አመቻቾች ተማሪ ተኮር የማስተማር ስነ-ዘዴን ተጠቅመዋል፣
- አመቻቾች የተለያዩ አደረጃጀቶችን በመጠቀም ተማሪዎች እንዲደጋገፉ አድርገዋል፣
- አመቻቾች ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የተለየ እገዛ አድርገዋል ።

**ምዘና**

**ስታንዳርድ 11**

አመቻቾች ተማሪዎቻቸውን በትክክል መዝነዋል፤ አስፈላጊውን ግብረ መልስ ሰጥተዋል።

**አመልካቾች፡-**

- የተከታታይ ምዘና ስርዓት ተዘርግቶ በጣቢያው ተተግብሯል፣
- አመቻቾች ተማሪዎቻቸውን መዝነው በወቅቱ ግብረ መልስ ሰጥተዋል፣
- አመቻቾች በምዘናው ውጤት መሰረት እገዛ አድርገዋል፣
- ጣቢያው የየደረጃውን ትምህርት ላጠናቀቁ ተማሪዎች የትምህርት ማስረጃ ሰጥቷል።

**ስታንዳርድ 12**

ጣቢያው የተደራጀ መረጃ ይዟል።

**አመልካቾች፡-**

- ጣቢያው የተማሪዎችንና የአመቻቾችን አጠቃላይ መረጃ አደራጅቶ ይዟል ፣
- ጣቢያው የተማሪዎችን የውጤት መረጃዎችና ስታትስቲክስ አደራጅቶ ይዟል፣
- ጣቢያው ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን የተመለከቱ መረጃዎችን መዝግቦ ይዟል።

### 5.1.1 ጣቢያው ከተማሪዎች፣ ከወላጆች/ ከአሳዳጊዎች ፣ ከህበረተሰቡና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ያለው ግንኙነት

**ስታንዳርድ 13**

ተማሪዎች ለጣቢያው በጎ አመለካከት አላቸው።

**አመልካቾች፡-**

- ተማሪዎች ጣቢያው በሚሰጣቸው አገልግሎት ረክተዋል።
- ተማሪዎች ጣቢያው ለሚያከናውኗቸው ሥራዎች ድጋፍ አድርገዋል።

**ስታንዳርድ 14**

ጣቢያው ከተማሪ ወላጆች/አሳዳጊዎች ፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት አለው ።

**አመልካቾች፡-**

- ህብረተሰቡ በጣቢያ የትምህርት አመራር ኮሚቴና "የአቋራጭ ተማሪዎች አስመላሽ ኮሚቴ" ንቁ ተሳትፎ ያደርጋል፣
- ጣቢያው ከወላጆች፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠሩ ድጋፍ አግኝቷል፣

- የወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ ተሳትፎ በመጨመሩ ጣቢያውን በባለቤትነት ስሜት የመምራት ልምድ ዳብሯል፣
- ህብረተሰቡ በጣቢያው የሥራ አፈፃፀም መርካቱን መረጃዎች ያመላክታሉ።

## 5.3 ውጤት /Output /

### 5.3.1 የትምህርት ተሳትፎና ፍትሃዊነት ግቦች ስኬት

**ስታንዳርድ 15**

ጣቢያው በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀመጡ የትምህርት ተሳትፎ የትምህርት ልማት ዘርፍ መርሃ ግብር ግቦችን አሳክቷል።

**አመልካቾች፡-**

- በጣቢያው አካባቢ የሚገኙ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናት (ከ7 -10 ዓመት) ሁሉ ወደ ጣቢያው እንዲመጡ ተደርጓል፣
- በጣቢያው አካባቢ የሚገኙ ዕድሜያቸው ከ11 እስከ 14 ዓመት የደረሱ ህፃናት ወደ ጣቢያው እንዲመጡ ተደርጓል።
- በጣቢያው የሴቶች ተሳትፎ ቁጥር ጨምሯል ።

### 5.3.2 የተማሪዎች ውጤትና ሥነ-ምግባር

**ስታንዳድ 16** የተማሪዎች ውጤት ተሻሽሏል።

**አመልካቾች፡-**

- ተማሪዎች ከደረጃ ወደ ደረጃ / ከክፍል ወደ ክፍል የሚዘዋወሩበት የእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነትና የሁሉም የትምህርት አይነቶች አማካይ ውጤት ከፍተኛ ነው፣
- የተማሪዎች የእጅ ፅሁፍ፣ የማንበብና የመሠረታዊ ስሌት ችሎታ ለደረጃው የሚመጥን መሆኑ ተረጋግጧል፣
- የተማሪዎች ውጤት በተከታታይ ዓመታት መሻሻል አሳይቷል።

**ስታንዳድ 17**

ተማሪዎች መልካም እሴቶችና ባህልን የተላበሱና አካባቢያቸውን የሚንከባከቡ መሆኑ በተግባር ተረጋግጧል።

**አመልካቾች**

- ተማሪዎች እርስ በርስ ተከባብረዋል፣
- ተማሪዎች ባህላቸውን ያከበራሉ፣
- ተማሪዎች የጣቢያውን ደንቦች አውቀው ስራ ላይ አውለዋል፣
- ተማሪዎች ጣቢያቸውንና አካባቢያቸውን ተንከባክበዋል።

# 6. የኢንስፔክሽን ሂደት

## 6.1 ለኢንስፔክሽን ተግባር የጣቢያዎች አመራረጥ

ጣቢያዎች ለኢንስፔክሽን ስራ በዋናነት የሚመረጡባቸው አካሄዶች ሁሉንም ጣቢያዎች በፍትሃዊነት ለማሳተፍ እንዲቻል አስተዳደራዊ መዋቅር፣ ስነምድራዊ አቅማመጥና የጣቢያዎች የብቃት ደረጃን ማእከል በማድረግ ይሆናል። ስብጥሩ የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑትን ያማከለ ይሆናል።

በየአመቱ ኢንስፔክሽን የሚካሄድባቸው ጣቢያዎች የሚመረጡት በክልል ትምህርት ቢሮ፤ በዞን / ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት (መምሪያ) እና በወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት በጋራ ወይም በየደረጃው በሚሰጥ ልዩ ትኩረት በሚሹ ጣቢያዎች ይሆናል። ለድጋፍና ክትትል ያመች ዘንድ የጋራ የኢንስፔክሽን ስራ የሚካሄድባቸውን ጣቢያዎች ሙሉ መረጃ እና የጊዜ ሰሌዳ ክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች ለትምህርት ሚኒስቴር በወቅቱ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል። ትምህርት ሚኒስቴርም እንደ አስፈላጊነቱ ጣቢያዎችን የሚያይበት አግባብ ሲፈጠር ከሚመለከተው ክልል /ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ጋር በጋራ ወይም በተናጠል የክትትልና ድጋፍ /የኢንስፔክሽን ስራ ያከናወናል።

## 6.2 የኢንስፔክሽን ቡድን አመሰራረት

የክልል ትምህርት ቢሮ፣ የዞን / ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት እና የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት የጣቢያዎችን ግምገማ ለማከናወን ሁለት አባላት ያሉት የኢንስፔክሽን ቡድን በማዋቀር ይከናወናል። ለኢንስፔክሽን የተሰማራው ቡድን ከአንድ ቀን በማያንስ ጊዜ በጣቢያው በመቆየት ተገቢውን የኢንስፔክሽን ተግባር ሊያከናውን ይገባል።

## 6.3 ከኢንስፔክሽን በፊት ከጣቢያዎች ጋር የሚደረግ ግንኙነት

የኢንስፔክሽን ስራ የሚከናወንባቸው ጣቢያዎች ከ15 ቀናት በፊት እንዲያውቁት ይደረጋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከታች የተመለከቱትን መረጃዎች አስቀድመው እንዲያዘጋጁም ይደረጋል።

- የጣቢያው የግለ ግምገማ ሰነድ፣
- ዓመታዊ የትምህርት ዕቅድ፣
- የተማሪዎችና የአመቻቾች መረጃ፣
- አገልግሎት መስጫ ክፍሎችን በተመለከተ አጠቃላይ መረጃ፣
- የትምህርት ክፍለ ጊዜ ስርጭትና የጊዜ ሰሌዳ፣
- የተማሪዎች ተከታታይ ምዘና የሚያሳይ የተጠናቀረ መረጃ፣
- በትምህርት ዙሪያ ለወላጆችና ለአካባቢው ማህበረሰብ ጣቢያውን አስመልክቶ የቀረቡ መሰረታዊ መረጃዎች፣

- በጣቢያው መጠናከር ዙሪያ ከአካባቢው ህብረተሰብ ጋር የተደረጉ ግንኙነቶችና የውይይት ቃለ ጉባኤዎች ፣
- የጣቢያውን የተለያዩ አደረጃጀቶች የሚያሳዩ ሰነዶች እና ሌሎች ተፈላጊ መረጃዎች ናቸው።

## 6.4 የኢንስፔክሽን አተገባበር

የኢንስፔክሽን ባለሙያዎች በጣቢያው እንደደረሱ ከተጠሪ አመቻች እና ሌሎች አመራሮች ጋር በመገናኘት ስለሚከናወነው የኢንስፔክሽን ስራ፣ ዓላማና አጠቃላይ ሁኔታ ገለፃ ካደረጉ በኋላ አመራሮቹን በመጋበዝ ጥያቄ/አስተያየት እንዲያቀርቡ ይደረጋል ። በተጨማሪም ተጠሪ አመቻቹ /ቿ ስለጣቢያው ነባራዊ ሁኔታ አጠቃላይ መረጃ፣ ጥንካሬና ድክመት በመግለጽ ትኩረት በሰጧቸው ጉዳዮች ላይ ገለፃ እንዲሰጡ ይደረጋል። የኢንስፔክሽን ቡድኑ በኢንስፔክሽን ወቅት ከጣቢያው ተጠሪ አመቻች ጋር በመገናኘት ከስራው ጋር ተያይዞ ለሚነሱ ጥያቄዎች እና ችግሮች በአፋጣኝ ለመፍታት የሚያስችል አማራጭ በማቅረብና ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር ችግሮቹን ለመፍታት ጥረት ያደርጋል።

## 6.5 የመረጃ አሰባሰብ ሂደት

የኢንስፔክሽን ቡድኑ ጣቢያዎችን አስመልክቶ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችለውን መረጃ ለመሰብሰብ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት ያከናውናል ።

- የሰነድ ምልከታ፣
- የምድረ ግቢ ምልከታ፣
- የክፍል ምልከታ ፣
- ከተጠሪ አመቻች፣ ከአመቻቾች እና ከተማሪዎች ጋር ውይይት ፣
- ከተማሪ ወላጆች / አሳዳጊዎች ጋር እና ከአካባቢው ማህበረሰብ ተወካዮች ጋር ውይይት በማድረግ ያከናውናል።

## 6.6 የመለኪያዎች ክብደት አሰጣጥ

የትምህርት ጥራትና ውጤታማነትን በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያ ደረጃ ለማረጋገጥ ከሚያስችሉ ስልቶች አንዱ የህብረተሰብን ተሳትፎ በማጎልበት ጣቢያዎችን በደረጃ በመለየት የውድድር መንፈስ በመፍጠር የአፈፃፀም ብቃታቸውን ወደላቀ ደረጃ ማድረስ ነው።

ከዚህ አኳያ የጣቢያዎችን ደረጃ ምደባ ለማከናወን በመለኪያነት ለተቀመጡት ለግብዓት፣ ለሂደት እና ለውጤት ክብደት በመስጠት እንደሚከተለው ይከናወናል።

| <u>**መለኪያዎች**</u> | <u>**ክብደት**</u> | |
|---|---|---|
| • **ለግብአት** /Input / | 30% | |
| • **ለሂደት** /Process/ | 40% | |
| • **ለውጤት**/Output/ | 30% | ድርሻ ተሰጥቷቸዋል። |

በተመሳሳይ ለግብአት፣ ለሂደትና ለውጤት በተሰጠው ክብደት መሰረት በስራቸው ለተቀመጡት ስታንዳርዶችና አመልካቾች ከይዘታቸው አኳያ ተከፋፍሎ በዚህ ሰነድ **በተቀጽላ** 2 ላይ ተመልክቷል። የኢንስፔክሽን ባለሙያዎች በአካል ተገኝተው በጣቢያው የሚገኙ መረጃዎችን በመፈተሽና ትንተና በማካሄድ ግምገማው ይከናወናል። በመቀጠልም የጣቢያው የትምህርት አቅርቦት የሚገኝበትን ደረጃ በመለየት የማሻሻያና የማጠናከሪያ ጠቋሚ ስልት በቅደም ተከትል ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

የወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት በጣቢያዎች የሚሰጠውን ትምህርት ጥራት የማስጠበቁ ሂደት በአግባቡ መከናወኑን በበላይነት ያስተባብራል፣ ይመራል፣ያረጋግጣል።

## 6.7 የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት

የጣቢያዎች ደረጃ አሰጣጥ ሂደት በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ በተመለከቱት ስታንዳርዶችና አመልካቾች መሰረት የሚከናወን ሆኖ ፥

- በተዘጋጀው የመረጃ መሰብሰቢያዎች/ቼክሊስት እና ገላጮችን /Descriptors /መሰረት በማድረግ ለእያንዳንዱ አመልካች /Indicator/ ውጤት በመስጠት ይከናወናል።
- በእያንዳንዱ ስታንዳርድ ውስጥ የሚገኙ አመልካቾች አማካይ ውጤት የስታንዳርዱ ውጤት ይሆናል።
- የግብዓት ስታንዳርድ አማካይ ውጤት የግብዓት ውጤት ይሆናል፣ የሂደትና የውጤት ስታንዳርድ አማካይ ውጤት በተመሳሳይ ሁኔታ ይሰላል።
- የግብአት፣ የሂደትና የውጤት አማካይ ድምር የጣቢያው ደረጃ ይሆናል።

በዚሁ መሰረት የሁሉም መለኪያዎች (በግብዓት፣ በሂደትና በውጤት) ድምር ውጤት

- ከ50% በታች ከሆነ ጣቢያው በደረጃ 1 ይመደባል፣
- ከ50% -69.99% በታች ከሆነ ጣቢያው በደረጃ 2 ይመደባል፣
- ከ70%-89.9% ከሆነ ጣቢያው በደረጃ 3 ይመደባል፣
- ከ90%-100% ከሆነ ጣቢያው ደረጃ 4 ይመደባል

የደረጃ አሰጣጥ ሂደት ዝርዝር አሰራሩ በዚህ ሰነድ መጨረሻ በተያዘው **ተቀጽላ** 3 ይመልከቱ። የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያው በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ የተቀመጡትን ስታንዳርዶች ማሟላቱን

በመገምገም አጠቃላይ የጣቢያውን የትምህርት አሰጣጥ ሂደት በሚከተሉት ደረጃዎች መሰረት ማጠቃለያ ድምዳሜ በኢንስፔክሽን ቡድኑ ይሰጣል።

- ደረጃውን ያላሟላ ጣቢያ ደረጃ 1
- ደረጃውን በማሻሻል ላይ ያለ ደረጃ 2
- ደረጃውን ያሟላ ደረጃ 3
- ደረጃውን በከፍተኛ ሁኔታ ያሟላ ደረጃ 4

የኢንስፔክሽን ቡድኑ ለስታንዳርዱ የተቀመጡ አመልካቾችን በመጠቀምና የተሰበሰቡ መረጃዎችን በማጠናቀር የጣቢያውን የአፈፃፀም ደረጃ የሚያሳይ ትክክለኛ ውሳኔ መስጠት ይጠበቅበታል።

ኢንስፔክተሮች ለእያንዳንዱ ስታንዳርድ የሰጡትን ውሳኔ በአራት ተመሳሳይ የደረጃ መለኪያዎች ይመዝናሉ። ይህም አጠቃላይ የሆነና ሁሉንም የተሰበሰቡ መረጃዎችን ጥቅም ላይ ያዋለ ሙያዊ ውሳኔ እንዲሰጡ ያስችላቸዋል። አንድ ጣቢያ በሶስት ዓመት አንድ ጊዜ በኢንስፔክሽን ቡድን መታየት ይኖርበታል። ጣቢያው በአጠቃላይ ውጤት መመዘኛውን ካላሟላ ወይም ከደረጃ ሶስት በታች ከሆነ መሻሻል የሚገባቸውን የትኩረት ነጥቦች በመለየትና ለሚመለከታቸው በማሳወቅ ከአንድ አመት በኋላ በኢንስፔክሽን በድጋሚ ይታያል። ሆኖም ጣቢያው የሚፈለገውን መሻሻል ካላመጣ በየደረጃው የሚመለከታቸው አካላት ተጠያቂ ይሆናሉ ።

## 6.8 ግብረ መልስ ስለ መስጠት

የኢንስፔክሽን ቡድኑ በክፍል ውስጥ ስለተደረጉ ምልከታዎች ለአመቻቹ/ቿ ግብረ መልስ መስጠት ይጠበቅበታል። የሚሰጡ ግብረመልሶች ገንቢ፣ በተማሪዎች ትምህርት አቀባበል፣ በትምህርት አሰጣጡ ወደፊት መሻሻል በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ያተኮረ መሆን ይኖርበታል ።

የኢንስፔክሽን ስራ ከተጠናቀቀ በኋላ ቡድኑ ለጣቢያው ተጠሪ አመቻች እና ሌሎች አመራሮች በኢንስፔክሽን ግኝት ስለተደረሰበት ውሳኔ እና ስለተሰጡ የመፍትሄ ሃሳቦች የቃልና የጽሁፍ ግብረመልስ መልስ ይሰጣል። ቡድኑ የሚሰጣቸው የመፍትሄ ሃሳቦችን ለማስተግበርና ድጋፍ ለማድረግ እንዲቻል በማጠቃለያ ውይይቱ ላይ የጉድኝት ማዕከሉ ሱፐርቫይዘር እንዲገኝ ይደረጋል።

## 6.9 የጽሁፍ ሪፖርት

የኢንስፔክሽን ቡድኑ ስራውን ካጠናቀቀ በኋላ በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ ተዘጋጅቶ በቀረበው የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ መሰረት የተገኙ ውጤቶችን፣ አስተያየቶችንና የመፍትሄ ሃሳቦችን አጠቃሎ የያዘ የጽሁፍ ሪፖርት ማዘጋጀት ይጠበቅበታል።

ኢንስፔክሽን ያካሄደው ቡድን ሪፖርቱን ከአስራ አምስት ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አጠናቅሮ ለጣቢያው፣ እንዲሁም ለወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት ያቀርባል። ጣቢያዎችም ለጣቢያው አጠቃላይ አባላትና

ለአካባቢው ማህበረሰብ በሪፖርቱ ላይ የቀረቡትን ሃሳቦች ማካፈልና በተለዩ ጉድለቶችም ላይ በጋራ መስራት ይኖርባቸዋል። የወረዳው ትምህርት ጽ/ቤትም እንደየደረጃው ለዞን ትምህርት ጽ/ቤት፣ ለክልልና/ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኢንስፔክሽን ዘርፍ የሚልኩ ሲሆን የክልሉ / ከተማ አስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ የተካሄዱ የኢንስፔክሽን አፈፃፀም ሪፖርቶችን በማጠቃለል ለትምህርት ሚኒስቴር የአጠቃላይ ትምህርት እንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት ይልካሉ።

### 6.10 ድጋፍና ክትትል ስለማድረግ

ግምገማው በሚከናወንበት ወቅት ደረጃውን ያሚሉና ከደረጃው በላይ ያገኙ ጣቢያዎች የበለጠ እንዲሻሻሉና በውጤታማነታቸው እንዲቀጥሉ ለማድረግ ክትትልና ድጋፍ ይደረግላቸዋል። ሆኖም የተቀመጠውን ስታንዳርድ ለማያሚሉ ጣቢያዎች በኢንስፔክተሮች የተሰጡ አስተያየቶችን መሰረት በማድረግ በጉድኝት ማዕከሉ የሚደረግ ተከታታይ ድጋፍ እንደተጠበቀ ሆኖ ተከታታይ ድጋፍና ክትትል በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ይደረግላቸዋል።

### 6.11 የቅሬታ አቀራረብ

ጣቢያው በኢንስፔክሽን ቡድኑ በተሰጠው ደረጃ ካልተስማማ ለሚመለከተው አካል ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል። በተሰጠው ምላሽ ካልረካ በሚቀጥለው ከፍተኛ አካል ጉዳዩ ሊታይ ይችላል። ቅሬታ የቀረበለት አካል ቅሬታ በቀረበባቸው ጉዳዮች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ በሚያስችል መልኩ የማረጋገጥና የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊ የሆኑ ማስተካከያዎች እንዲያደርጉ በተጨባጭ ማስረጃ ላይ ተመርኩዞ ማከናወን ይጠበቅበታል።

## 7 የኢንስፔክተሮች ሙያዊ ስነ-ምግባር

**ማንኛውም ኢንስፔክተር ፦**

- በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ ውስጥ ለሚከናወኑ ተግባራት ሙያዊ አቀራረብ እንዲኖረው ይጠበቃል ፣
- ከጣቢያው ማህበረሰብ ጋር የሚያደርጋቸው ውይይቶችና ግንኙነቶች በመከባበር ላይ የተመሰረቱ ሊሆን ይገባል፣
- በተቻለ መጠን የጣቢያውን መማር ማስተማር ሳይስተጓጉል ስራውን ለማከናወን ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል፣
- በሀገር አቀፍ የኢንስፔክሽን መመሪያ መሠረት ሥራውን ያከናውናል፣

- የሚሰጣቸው ውሳኔዎች በተጨባጭ መረጃና ሚዛናዊነቱን በጠበቀ መልኩና ግልፅነት በተሞላበት ሁኔታ ማከናወን ይኖርበታል፣
- ከአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ ማህበረሰብ ጋር የሚያካሂዳቸው ውይይቶች ጣቢያውን የሚገነባና መሻሻልን ሊያመጣ የሚችል እንጂ ስህተት ፈላጊ መሆን የለበትም፣
- የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል የሚሰጣቸው አስተያየቶች የሚኖራቸው አስተዋጽኦ እንደተጠበቀ ሆኖ በስራ አጋጣሚ የሰበሰባቸው መረጃዎች ሚስጥር የመጠበቅ ሃላፊነትና ግዴታ አለበት፣
- ገለልተኛ ሆኖ በተጨባጭ መረጃዎች ላይ በመመስረት መረጃዎችን በማሰባሰብ የውሳኔ ሀሳቦችን ያቀርባል።

## ተቀጽላ-1 (APPENDIX) የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ኢንስፔክሽን ስታንዳርዶችና አመልካቾች

### 1.ግብአት (Input) 30%

| ትኩረት መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች/Indicators/ | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| **የጣቢያው ፋሲሊቲ፣ የመማሪያና የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች ፣ የሰው ኃይልና የገንዘብ ምንጮች** | 1. ጣቢያው ለደረጃው በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የመማሪያና የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፣ የማስፈጸሚያ ሰነዶች፣ የመጫወቻ ቁሳቁሶች አሟልቷል። 8% | • የጣቢያው የመማሪያና አገልግሎት መስጫ ክፍሎች በተቀመጠላቸው ስታንዳርድ መሰረት ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ማስተናገድ በሚችል መልኩ (በቂ ብርሃን፣ ስፋት፣ወለል ወዘተ) የተሰሩና የተሟሉ ናቸው፣2%<br>• ጣቢያው በስታንዳርዱ መሰረት የተማሪ መጽሐፍት ጥምርታ ፣ የተማሪ-ክፍል ጥምርታ፣ የተማሪ- አመቻች ጥምርታ፣ የአመቻቹ/ቿ መምሪያ ፣ አጋዥ/ ማጣቀሻ መጽሐፍትና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን አሟልቷል፣2%<br>• በጣቢያው ሀገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ ልዩ ልዩ መመሪያዎች፣ ሀገራዊና ክልላዊ ፕሮግራሞችና ማዕቀፎች፣ የጣቢያው ደንብ ወዘተ ተሟልቷል፣ 2%<br>• ጣቢያው በስታንዳርዱ መሠረት የመጫወቻ ቦታ፣ ቁሳቁሶች እና ሌሎች ፋሲሊቲዎችን አሟልቷል። 2% | • የጣቢያው ህንፃና የመማሪያ ክፍሎቹን በመመልከት፣<br>• የጣቢያው የተለያዩ ፋሲሊቲዎች/ ቁሳቁሶች/ በመቁጠር፣<br>• ተማሪዎችን፣ ርእሰ የአመቻቹ/ቿ የሚመለከታቸውን የወረዳ ት/ፅ/ቤት ሠራተኞች በመጠየቅ። ሰነዶችን በመመልከት |
| | 2 የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማሻሻል ጣቢያው አስፈላጊ የሃብት ምንጮች አሰባስቧል። 6% | • ጣቢያው የድጎማ በጀቱን (School grant) ተቀብሏል፣1%<br>• ጣቢያው ጥቅል በጀቱን (Block grant) ተቀብሏል፣1%<br>• ጣቢያው ከወላጆችና ከአካባቢው ማህበረሰብ ሃብት (በገንዘብ፣ በዓይነትና በጉልበት) አሰባስቧል፣2%<br>• ጣቢያው በአካባቢው ከሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ሃብት አሰባስቧል፣2% | ስለ ጣቢያው የሃብት ምንጭና አጠቃቀም የሚያሳዩ ሰነዶች፣ |

| ትኩረት መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች/Indicators/ | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| | 3. ጣቢያው ለደረጃው የሚመጥኑ ተጠሪ አመቻችና አመቻቾች በስታንዳርዱ መሰረት አሟልቷል። 4% | • ጣቢያው በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ማስረጃ ያለው/ያላት ተጠሪ አመቻች አለው፣ 2%<br>• ጣቢያው በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ማስረጃ ያላቸው አመቻቾች አሉት። 2% | የአመቻች ፕሮፋይል የሚያሳይ መዝገብ፣ ከወረዳ ት/ፅ/ቤት ጋር በመወያየት፣ |
| ምቹ የመማሪያ አካባቢ | 4. ጣቢያው ለህፃናቱ ቅርብ፣ ምቹና ለደህንነታቸው የማያሰጋ ነው።12% | • የትምህርት መስጫ ጣቢያውን ማስከበር የሚችል አጥር ተሰርቷል፣ 2%<br>• ጣቢያው በስታንዳርዱ መሠረት ተፈላጊውን የቦታ ስፋት አሟልቷል፣2%<br>• በጣቢያው የሚገኙ የመማሪያ ክፍሎችና አገልግሎት መስጫዎች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን አካቶ ለማስተማር ምቹ ነው፣2%<br>• ጣቢያው ለህፃናት ምቹና የመማር ማስተማሩን ሂደት ከሚያውኩና በህፃናት ላይ አደጋ ሊያስከትሉ ከሚችሉ (አውሬ፣ ገደል፣ ጎርፍ. ወዘተ…) የራቀ ነው፣2%<br>• ጣቢያው በፆታ የተለየ መፀዳጃ ቤት አለው፣2%<br>• ጣቢያው የውሃ አገልግሎት አለው።2% | • ምድረ ግቢውን በመመልከት<br>• መረጃዎችን በመመልከት<br>• ክፍሎችን በመመልከት፣<br>• ጥገናን የሚመለከቱ ሪከርዶች<br>• ደህንነትን የተመለከቱ ሪፖርቶች<br>• የጣቢያውን ማህበረሰብ በማወያየት |
| **ሂደት** /Process / 40 % | | | |
| ሥርዓተ ትምህርት፣ መማር፣ ማስተማር ፣ ምዘና | 5.በጣቢያው የሚሰጠው ትምህርት በአገር አቀፍ ወይም በክልሉ በተዘጋጀው የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት / በመደበኛው ሥርዓተ ትምህርት መሰረት ነው። 2% | • ጣቢያው የሚጠቀምበት የተማሪዎች መፅሐፍትና የአመቻቾች መምሪያ ሥርዓተ ትምህርቱን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ነው፣ 1%<br>• አመቻቾች የሚያስተምሩት ትምህርት በሥርዓተ ትምህርቱ መሰረት ነው።1% | • የጣቢያውን ማህበረሰብ በማወያየት<br>• የክፍል ውስጥ ምልከታ |

| ትኩረት መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች/Indicators/ | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| | 6. ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ንቁ ተሳትፎ አድርገዋል። 4% | • ተማሪዎች የተሰጧቸውን ሥራዎች በትጋት ይሰራሉ፣ 2%<br>• ተማሪዎች ጥያቄዎችን በመጠየቅና መልሶችን በመመለስ የነቃ ተሳትፎ አድርገዋል፣ 1%<br>• ተማሪዎች በተለያዩ አደረጃጀቶች በመሳተፍ እርስ በርስ ተደጋግፈዋል፣1% | • የጣቢያውን ማህበረሰብ በማወያየት<br>• የክፍል ውስጥ ምልከታ |
| | 7.ተማሪዎች በትምህርት አቀባበላቸው መሻሻል አሳይተዋል። 5% | • ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እየተማሩ ነው፣1%<br>• ተማሪዎች የትምህርት ጊዜያቸውን ሳያባክኑ በአግባቡ ተጠቅመዋል፣1%<br>• የክፍል ደረጃውን የሚመጥን የእጅ ጽሁፍ፣ የማንበብና የመሠረታዊ ስሌት ችሎታ አላቸው፣2%<br>• ተማሪዎች ለሚማሯቸው ትምህርቶች ተመጣጣኝ ክብደት ይሰጣሉ፣1% | • የጣቢያውን ማህበረሰብ በማወያየት<br>• የክፍል ውስጥ ምልከታ |
| | 8. የጣቢያው ትምህርት ፕሮግራም አደረጃጀት በተቀመጠው ስታንዳርድና የአካባቢው ህብረተሰብ አኗኗርን ያገናዘበ ነው። 2% | • የጣቢያው ዓመታዊ፣ ሳምንታዊና ዕለታዊ የትምህርት ፕሮግራም በስታንዳርዱ መሰረት የተዘጋጀ ነው፣1%<br>• የትምህርቱ አሰጣጥ የህብረተሰቡ አኗኗርን መሰረት ያደረገ ነው ።1% | • የጣቢያውን ማህበረሰብ በማወያየት<br>• የክፍል ውስጥ ምልከታ |
| | 9. አመቻቾች የሚያስተምሩት ትምህርት በአግባቡ የታቀደና በትምህርት መርጃ መሳሪያዎች የተደገፈ ነው።7% | • አመቻቾች ትምህርቱን በዓመት፣ በሴሚስተር፣ በሣምንት/ በቀንና በክፍለ ጊዜያት/ ከፋፍለው አቅደዋል፣ 2%<br>• አመቻቾች ከትምህርቱ ይዘት ጋር የተጣጣመ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ተጠቅመዋል፣ 1%<br>• አመቻቾች ተማሪዎቻቸው በትምህርታቸውና በውጤታቸው እንዲሻሻሉ የማጠናከሪያ ትምህርት በመስጠት እገዛ አድርገዋል፣ 2%<br>• አመቻቾች ለሴት ተማሪዎች የተለየ እገዛ አድርገዋል። 2% | • የጣቢያውን ማህበረሰብ በማወያየት<br>• የክፍል ውስጥ ምልከታ |

| ትኩረት መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች/Indicators/ | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| | 10.አመቻቾች አሳታፊ የማስተማር ዘዴ ተጠቅመዋል። 4% | • አመቻቾች ተማሪ ተኮር የማስተማር ስነ-ዘዴን ተጠቅመዋል፣ 2%<br>• አመቻቾች የተለያዩ አደረጃጀቶችን በመጠቀም ተማሪዎች እንዲደጋገፉ አደርገዋል፣ 1%<br>• አመቻቾች ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የተለየ እገዛ አድርገዋል፣ 1% | የጣቢያውን ማህበረሰብ በማወያየት<br>የክፍል ውስጥ ምልከታ<br>ሰነዶችን በመመልከት |
| | 11.አመቻቾች ተማሪዎቻቸውን በትክክል መዝነዋል፤ አስፈላጊውን ግብረ መልስ ሰጥተዋል።5% | • የተከታታይ ምዘና ስርዓት ተዘርግቶ በጣቢያው ተተግብሯል፣ 2%<br>• አመቻቾች ተማሪዎቻቸውን መዝነው በወቅቱ ግብረ መልስ ሰጥተዋል፣ 1%<br>• አመቻቾች በምዘናው ውጤት መሰረት እገዛ አድርገዋል፣1%<br>• ጣቢያው የየደረጃውን ትምህርት ላጠናቀቁ ተማሪዎች የትምህርት ማስረጃ ሰጥቷል።1% | • የጣቢያውን ማህበረሰብ በማወያየት<br>• የክፍል ውስጥ ምልከታ<br>• ሰነዶችን በመመልከት |
| | 12. ጣቢያው የተደራጀ መረጃ ይዟል።3% | • ጣቢያው የተማሪዎችንና የአመቻቾችን አጠቃላይ መረጃ አደራጅቶ ይዟል ፣1%<br>• ጣቢያው የተማሪዎችን የውጤት መረጃዎችና ስታትስቲክስ አደራጅቶ ይዟል፣1%<br>• ጣቢያው ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን የተመለከቱ መረጃዎችን መዝግቦ ይዟል።1% | • ሰነዶችን በመመልከት<br>• የጣቢያውን ማህበረሰብ በማወያየት<br>• የክፍል ውስጥ ምልከታ |
| **ጣቢያው ከተማሪዎች፣ ከወላጆች/ ከአሳዳጊዎች ፣ ከህበረተሰቡና ከአጋር ደርጅቶች ጋር ያለው ግንኙነት** | 13. ተማሪዎች ለጣቢያው በጎ አመለካከት አላቸው። 4% | • ተማሪዎች ጣቢያው በሚሰጣቸው አገልግሎት ረክተዋል። 2%<br>• ተማሪዎች ጣቢያው ለሚያከናውናቸው ሥራዎች ድጋፍ አድርገዋል፣2% | • የጣቢያውን ማህበረሰብ በማወያየት<br>• የክፍል ውስጥ ምልከታ<br>• ሰነዶችን በመመልከት |

| ትኩረት መስክ (Aspect) | ስታንዳርድ | አመልካቾች/Indicators/ | የመረጃ ምንጮች |
|---|---|---|---|
| | 14. ጣቢያው ከተማሪ ወላጆች/አሳዳጊዎች ፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት አለው ። 4% | • ህብረተሰቡ በጣቢያ የትምህርት አመራር ኮሚቴና "የአቋራጭ ተማሪዎች አስመላሽ ኮሚቴ" ንቁ ተሳትፎ ያደርጋል፣1%<br>• ጣቢያው ከወላጆች፣ ከአካባቢው ማህበረሰብና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠሩ ድጋፍ አግኝቷል፣1%<br>• የወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ ተሳትፎ በመጨመሩ ጣቢያውን በባለቤትነት ስሜት የመምራት ልምድ ዳብሯል፣1%<br>• ህብረተሰቡ በጣቢያው የሥራ አፈፃፀም መርካቱን መረጃዎች ያመላክታሉ።1% | • የጣቢያውን ማህበረሰብ በማወያየት<br>• የክፍል ውስጥ ምልከታ<br>• ሰነዶችን በመመልከት |
| **ውጤት /Output / 30 %** | | | |
| የትምህርት ተሳትፎና ፍትሃዊነት ግቦች ስኬት | 15. ጣቢያው በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀመጡ የትምህርት ተሳትፎ የትምህርት ልማት ዘርፍ መርሃ ግብር ግቦችን አሳክቷል። 9% | • በጣቢያው አካባቢ የሚገኙ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናት (ከ7 -10 ዓመት) ሁሉ ወደ ጣቢያው እንዲመጡ ተደርጓል፣3%<br>• በጣቢያው አካባቢ የሚገኙ ዕድሜያቸው ከ11 እስከ 14 ዓመት የደረሱ ህፃናት ወደ ጣቢያው እንዲመጡ ተደርጓል።3%<br>• በጣቢያው የሴቶች ተሳትፎ ቁጥር ጨምሯል ። 3% | • የጣቢያውን ማህበረሰብ በማወያየት<br>• የክፍል ውስጥ ምልከታ<br>• ሰነዶችን በመመልከት |
| **የተማሪዎች ውጤትና ሥነ-ምግባር** | 16. የተማሪዎች ውጤት ተሻሽሏል።12% | • ተማሪዎች ከደረጃ ወደ ደረጃ / ከክፍል ወደ ክፍል የሚዘዋወሩበት የእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነትና የሁሉም የትምህርት አይነቶች አማካይ ውጤት ከፍተኛ ነው፣ 4%<br>• የተማሪዎች የእጅ ፅሁፍ፣ የማንበብና የመሠረታዊ ስሌት ችሎታ ለደረጃው የሚመጥን መሆኑ ተረጋግጧል፣/4%/<br>• የተማሪዎች ውጤት በተከታታይ ዓመታት መሻሻል አሳይቷል።/4%/ | • ተጠሪ አመቻቾችንና ወላጆችን በማወያየት<br>• የክፍል ውስጥ ምልከታ |
| | 17. ተማሪዎች መልካም እሴቶችና ባህልን የተላበሱና አካባቢያቸውን የሚንከባከቡ መሆኑ በተግባር ተረጋግጧል።9% | • ተማሪዎች እርስ በርስ ተከባብረዋል፣2%<br>• ተማሪዎች ባህላቸውን ያከበራሉ፣2%<br>• ተማሪዎች የጣቢያውን ደንቦች አውቀው ስራ ላይ አውለዋል፣2%<br>• ተማሪዎች ጣቢያቸውንና አካባቢያቸውን ተንከባክበዋል።3% | • የጣቢያውን ማህበረሰብ በማወያየት |

**ተቀጽላ-2 ፣ ገላጮች** / DESCRIPTORS /

**ቁልፍ** / key / ፡- በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ ውሳኔ ሰጪው አካል ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ተገንዝቦ ውሳኔ እንዲሰጥ ይጠበቃል። እንደ አጠቃላይ በዚህ ሰነድ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉና በአተረጓጎም ተመሳሳይነት እንዲኖራቸው ታስቦ በመስፈርትነት የተቀመጡ ቃላቶች ከዚህ በታች ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል።

- ከፍተኛ እጥረት/በጣም ዝቅተኛ/አነስተኛ /ውሱን ማለት ከሚጠበቀው ስታንዳርድ አንጻር ከ50 በመቶ በታች ያገኘ፣
- አብዛኛው/አብዛኞቹ/ከፍተኛ ማለት ከሚጠበቀው ስታንዳርድ አንጻር 50-69.99 በመቶ ያገኘ፣
- ሙሉ በሙሉ/ሁሉንም ማለት ከሚጠበቀው ስታንዳርድ 70-89.99 በመቶ ያገኘ፣
- በጣም ከፍተኛ የሚለው 90 ከመቶ እና በላይ ያገኘ፣

በሚል በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል።

| ግብዓት / 30% / | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **ስታንዳርድ 1** ጣቢያው ለደረጃው በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የመማሪያና የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፣ የማስፈጸሚያ ሰነዶች፣ የመጫወቻ ቁሳቁሶች አሟልቷል።8% | | | | |
| **አመልካች** | **ደረጃ 1**<br>**ደረጃውን ያላሟላ** | **ደረጃ 2**<br>**ደረጃውን በማሻሻል ላይ ያለ** | **ደረጃ 3**<br>**ደረጃውን ያሟላ** | **ደረጃ 4**<br>**ደረጃውን በከፍተኛ ደረጃ ያሟላ** |
| 1.1 የጣቢያው የመማሪያና አገልግሎት መስጫ ክፍሎች በተቀመጠላቸው ስታንዳርድ መሰረት ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ማስተናገድ በሚችል መልኩ (በቂ ብርሃን፣ ስፋት፣ወለል ወዘተ) የተሰሩና የተሟሉ ናቸው፣2% | ጣቢያው በስታንዳርዱ መሰረት የተሰሩ የመማሪያና የአገልግሎት መስጫ ክፍሎችየሉትም፤ | ጣቢያው በስታንዳርዱ መሰረት የተሰሩ የመማሪያና የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች በአብዛኛው የሉትም፤ | የጣቢያውየመማሪያና የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች በስታንዳርዱ መሰረት የተሰሩ ናቸው፤ | የጣቢያው የመማሪያና የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች ከስታንዳርዱ በላይ የተሟሉ ናቸው፤ |
| 1.2 ጣቢያው በስታንዳርዱ መሰረት የተማሪ መጽሐፍት ጥምርታ፣ የተማሪ-ክፍል ጥምርታ፣ የተማሪ- አመቻች ጥምርታ፣ የአመቻቹ/ቿ መምሪያ፣ አጋዥ/ ማጣቀሻ መጽሐፍትና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን አሟልቷል፣2% | ጣቢያው ለመማር ማስተማር ስራ የሚያገለግሉ የተማሪ መፃህፍት፣ የአመቻቹ/ቿ መምሪያ እና አጋዥ/ ማጣቀሻ መጽሃፍት፣ የሉትም። | ጣቢያው ለመማር ማስተማር ስራ የሚያገለግሉ የተማሪ መፃህፍት፣ የአመቻቹ/ቿ መምሪያ እና አጋዥ/ ማጣቀሻ መጽሃፍት፣ ከፍተኛ እጥረት አለበት፤ | ጣቢያው ለመማር ማስተማር ስራ የሚያገለግሉ የተማሪ መፃህፍት፣ የአመቻቹ/ቿ መምሪያ እና አጋዥ/ ማጣቀሻ መጽሃፍት በስታንዳርዱ መሰረት አሟልቷል፤ | ጣቢያው ለመማር ማስተማር ስራ የሚያገለግሉ የተማሪ መፃህፍት፣ የአመቻቹ/ቿ መምሪያ እና አጋዥ/ ማጣቀሻ መጽሃፍት፣ ለስታንዳርዱ በላይ አሟልቷል፤ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1.3 በጣቢያው ሀገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ ልዩ ልዩ መመሪያዎች፣ ሀገራዊና ክልላዊ ፕሮግራሞችና ማዕቀፎች፣ የጣቢያው ደንብ ወዘተ ተሟልቷል፣ 2% | በጣቢያው ሀገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ መመሪያዎች፣ አገራዊና ክልላዊ ፕሮግራሞችና ማእቀፎች፣ ህገ መንግስት፣ የጣቢያው ደንብ ወዘተ የሉትም፤ | በጣቢያው ሀገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ መመሪያዎች፣ አገራዊና ክልላዊ ፕሮግራሞችና ማእቀፎች፣ ህገ መንግስት፣ የጣቢያው ደንብ ወዘተ በአብዛኛው አልተሟሉም፤ | በጣቢያው ሀገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ መመሪያዎች፣ አገራዊና ክልላዊ ፕሮግራሞችና ማእቀፎች፣ ህገ መንግስት፣ የጣቢያው ደንብ ወዘተ ተሟልተዋል፣ | በጣቢያው ሀገር አቀፍ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ መመሪያዎች፣ አገራዊና ክልላዊ ፕሮግራሞችና ማእቀፎች፣ ህገ መንግስት፣ የጣቢያው ደንብ ወዘተ ስታንዳርዱ ካስቀመጣቸው ቁጥሮች በላይ ተሟልተዋል፤ |
| 1.4 ጣቢያው በስታንዳርዱ መሠረት የመጫወቻ ቦታ፣ ቁሳቁሶች እና ሌሎች ፋሲሊቲዎችን አሟልቷል። 2% | ጣቢያው ስታንዳርዱ ያስቀመጣቸውን የመጫወቻ ቁሳቁሶች እና ሌሎች ፋሲሊቲዎችን አላሟላም፤ | ጣቢያው ስታንዳርዱ ያስቀመጣቸውን የመጫወቻ ቁሳቁሶች እና ሌሎች ፋሲሊቲዎችን በአብዛኛው አላሟላም፤ | ጣቢያው ስታንዳርዱ ያስቀመጣቸውን የመጫወቻ ቁሳቁሶች እና ሌሎች ፋሲሊቲዎችን አሟልቷል፤ | ጣቢያው ስታንዳርዱ ካስቀመጠው ቁጥር በላይ የመጫወቻ ቁሳቁሶች እና ሌሎች ፋሲሊቲዎችን አሟልቷል፤ |

**ስታንዳርድ 2 የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማሻሻል ጣቢያው አስፈላጊ የሃብት ምንጮች አሰባስቧል። 6%**

| **አመልካች** | **ደረጃ 1**<br>**ደረጃውን ያላሟላ** | **ደረጃ 2**<br>**ደረጃውን በማሻሻል ላይ ያለ** | **ደረጃ 3**<br>**ደረጃውን ያሟላ** | **ደረጃ 4**<br>**ደረጃውን በከፍተኛ ደረጃ ያሟላ** |
|---|---|---|---|---|
| 2.1 ጣቢያው የድጎማ በጀቱን (School grant) ተቀብሏል፣ 1% | ጣቢያው የሚገባውን ድጐማ አልተቀበለም፤ | ጣቢያው ድጐማ የደረሰው ቢሆንም ለታለመለት አላማ አላዋለውም፤ | ጣቢያውየሚገባውን ድጐማ ተቀብሎ ሙሉ በሙሉ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት አውሏል | ጣቢያውየሚገባውን ድጐማ ተቀብሎ ሙሉ በሙሉ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት አውሏል፤ ተጨማሪ በጀት ከተለያዩ ምንጮች በማፈላለግ ሌሎች ተግባራትን አከናውኗል፤ |
| 2.2 ጣቢያው ጥቅል በጀቱን (Block grant) ተቀብሏል፣/1%/ | ጣቢያው የሚገባውን ጥቅል በጀት አልተቀበለም፤ | ጣቢያው የሚገባውን ጥቅል በጀት የደረሰው ቢሆንም ለታለመለት አላማ አላዋለውም፤ | ጣቢያው የሚገባውን ጥቅል በጀት ተቀብሎ ሙሉ በሙሉ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት አውሏል፤ | ጣቢያው የሚገባውን ጥቅል በጀት ተቀብሎ ሙሉ በሙሉ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት አውል፤ ተጨማሪ በጀት ከተለያዩ ምንጮች በማፈላለግ ሌሎች ተግባራትን አከናውኗል፤ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 2.3 ጣቢያው ከወላጆችና ከአካባቢው ማህበረሰብ ሃብት (በገንዘብ፣ በዓይነትና በጉልበት) አሰባስቧል፣ 2% | ጣቢያው ከወላጆችና ከአካባቢው ማህበረሰብ ሃብት አላሰባሰበም፤ | ጣቢያው ከወላጆችና ከአካባቢው ማህበረሰብ ሃብት በከፊል አሰባስቧል። | ጣቢያው ከወላጆችና ከአካባቢው ማህበረሰብ መሰብሰብ የሚገባውን ሃብት አሰባስቧል፤ | ጣቢያው ከወላጆችና ከአካባቢው ማህበረሰብ ሃብት ከሚጠበቀው በላይ አሰባስቧል። ከማሰባሰቡ በተጨማሪ ለሚፈለገው ዓላማ ጥቅም ላይ አውሏል፤ |
| 2.4 ጣቢያው በአካባቢው ከሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ሃብት አሰባስቧል፣ 2% | ጣቢያው በአካባቢው ከሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ሃብት አላሰባሰበም። | ጣቢያው በአካባቢው ከሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ሃብት በአብዛኛው አሰባስቧል። | ጣቢያው በአካባቢው ከሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ሃብት አሰባስቧል፤ | ጣቢያው በአካባቢው ከሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ከሚጠበቀው በላይ ሃብት አሰባስቧል። ለታለመለት ዓላማ አውሏል፤ |
| **ስታንዳርድ 3 ጣቢያው ለደረጃው የሚመጥኑ ተጠሪ አመቻችና አመቻቾች በስታንዳርዱ መሰረት አሟልቷል። 4%** | | | | |
| **አመልካች** | **ደረጃ 1 ደረጃውን ያላሟላ** | **ደረጃ 2 ደረጃውን በማሻሻል ላይ ያለ** | **ደረጃ 3 ደረጃውን ያሟላ** | **ደረጃ 4 ደረጃውን በከፍተኛ ደረጃ ያሟላ** |
| 3.1 ጣቢያው በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ማስረጃ ያለው/ያላት ተጠሪ አመቻች አለው፣ 2% | ጣቢያው ተጠሪ አመቻች የለውም፤ | ጣቢያው በስታንዳርዱ መሰረት ተጠሪ አመቻች ያለው ቢሆንም የትምህርት ደረጃውን ያሟላ/ያሟላች አይደለም። | ጣቢያው በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ደረጃ ያለው / ያላት ተጠሪ አመቻች አለው፤ | የጣቢያው ተጠሪ አመቻች በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ደረጃውን ከማሟላቱ/ቷ በተጨማሪ በርካታ ስልጠናዎችን የወሰደ/ች መሆኑ ተረጋግጧል፤ |
| 3.2 ጣቢያው በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ማስረጃ ያላቸው አመቻቾች አሉት። 2% | ጣቢያው በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ደረጃ ያላቸው አመቻቾች የሉትም። | አብዛኛው የጣቢያው አመቻቾች በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ደረጃ ያላቸው ናቸው። | ሁሉም የጣቢያው አመቻቾች በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ደረጃ ያላቸው ናቸው። | የጣቢያው አመቻቾች በስታንዳርዱ መሰረት የትምህርት ደረጃ ከማሟላታቸው በተጨማሪ ራሳቸውን ለማብቃትና ወቅታዊ ለማድረግ ስልጠና ወስደዋል፤ |

| ስታንዳርድ 4 ጣቢያው ለህፃናቱ ቅርብ፣ ምቹና ለደህንነታቸው የማያሰጋ ነው።12% | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አመልካች | ደረጃ 1<br>ደረጃውን ያላሟላ | ደረጃ 2<br>ደረጃውን በማሻሻል ላይ ያለ | ደረጃ 3<br>ደረጃውን ያሟላ | ደረጃ 4<br>ደረጃውን በከፍተኛ ደረጃ ያሟላ |
| 4.1 የትምህርት መስጫ ጣቢያውን ማስከበር የሚችል አጥር ተሰርቷል፣ 2% | ጣቢያው በአጥር አልተከለለም። | ጣቢያው በከፊል በአጥር ተከልሏል። | የጣቢያው ግቢ በስታንዳርዱ መሰረት በአጥር ተከበሯል፤ | የትምህርት መስጫ ጣቢያው በአጥር ከመከበሩ በተጨማሪ ወቅታዊ ጥገና ይደረግለታል። |
| 4.2 ጣቢያው በስታንድርዱ መሠረት ተፈላጊውን የቦታ ስፋት አሟልቷል፣ 2% | ጣቢያው ከፍተኛ የሆነ የቦታ ጥበት አለበት። | ጣቢያው ያለው የቦታ ስፋት ወደ ስታንዳርዱ የቀረበ ነው። | ጣቢያውተፈላጊውን የቦታ ስፋት በስታንድርዱ መሠረት አሟልቷል፤ | ጣቢያው ተፈላጊውን የቦታ ስፋት በስታንድርዱ መሠረት ከማሟላቱ በተጨማሪም ለውስጥ ገቢ ይጠቀምበታል። |
| 4.3 በጣቢያው የሚገኙ የመማሪያ ክፍሎችና አገልግሎት መስጫዎች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን አካቶ ለማስተማር ምቹ ነው፣2% | የጣቢያው የመማሪያና አገልግሎት መስጫዎች ክፍሎች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን አካቶ ለማስተማር ምቹ አይደሉም። | አብዛኛዎቹ የጣቢያው የመማሪያና አገልግሎት መስጫዎች ክፍሎች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን አካቶ ለማስተማር ምቹ ናቸው። | የጣቢያው የመማሪያና አገልግሎት መስጫዎች ክፍሎች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን አካቶ ለማስተማር ምቹ ናቸው። | የጣቢያው የመማሪያና አገልግሎት መስጫዎች ክፍሎች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን አካቶ ለማስተማር ምቹ ከመሆናቸውም ባሻገር በአካባቢው በሞዴልነት መጠቀስ የሚችሉ ናቸው። |
| 4.4 ጣቢያው ለህፃናት ምቹና የመማር ማስተማሩን ሂደት ከሚያውኩና በህፃናት ላይ አደጋ ሊያስከትሉ ከሚችሉ (አውሬ፣ ገደል፣ ጎርፍ. ወዘተ...) የራቀ ነው። 2% | ጣቢያው ለህፃናት ምቹ ካለመሆኑ በተጨማሪ የመማር ማስተማሩን ሂደት ከሚያውኩና አደጋ ሊያስከትሉ ከሚችሉ የራቀ አይደለም፤ | ጣቢያው ለህፃናት ምቹ ቢሆንም የመማር ማስተማሩን ሂደት ከሚያውኩ ነገሮች የራቀ አይደለም። | ጣቢያው ለህፃናት ምቹ የሆነ፣ የመማር ማስተማሩን ሂደት ከሚያውኩና አደጋ ሊያስከትሉ ከሚችሉ ነገሮች የራቀ ነው። | ጣቢያው ለህፃናት ምቹ የሆነ፣ የመማር ማስተማሩን ሂደት ከሚያውኩና አደጋ ሊያስከትሉ ከሚችሉ የራቀ ከመሆኑም ባሻገር በአካባቢው ህብረተሰብ ተመራጭ መሆን ችሏል፤ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 4.5 ጣቢያው በፆታ የተለየ መፀዳጃ ቤት አለው።2% | ጣቢያው መፀዳጃ ቤት የለውም፤ | ጣቢያው መፀዳጃ ቤት ያለው ቢሆንም በፆታ የተለየ አይደለም። | ጣቢያው በፆታ የተለየ መፀዳጃ ቤት አለው። | ጣቢያው በፆታ የተለየና ንጽሕናውን የጠበቀ መፀዳጃ ቤት አለው፤ |
| 4.6 ጣቢያው የውሃ አገለግሎት አለው።2% | ጣቢያው የውሃ አገልግሎት የለውም። | ጣቢያው የውሃ አገለግሎት ያለው ቢሆንም ከጣቢያው ማኅበረሰብ ቁጥር አኳያ በቂ አይደለም። | ጣቢያው ለጣቢያው ማኅበረሰብ በቂ የሆነ የተሟላ የውሃ አገለግሎት አለው። | ጣቢያው በየወቅቱ የሚታከም የውሃ አገልግሎት ያለው ከመሆኑም በተጨማሪ ለመጠባበቂያ የውሃ ታንከር /Reservoir/ አለው፤ |
